# በስቶክሆልም ለታላቁ የኀዳሴ ግድብ የገቢ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀው ፕሮግራም በደመቀ ሁኔታታ ተካሄደ::

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ በስቶክሆልም ለታላቁ የኀዳሴ ግድብ ገቢ አሰባሳቢ ም/ቤት ያዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም መስከረም 4/2006 ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ ተካሂዷል::



በስቶክሆልም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ቆ/ጄ/ጽ/ቤት ቆንስል ጄኔራል ወ/ሮ መብራት በየነ በእለቱ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያውያኖችና ትውልደ ኢትዮጵያውያኖች ለታላቁ ኀዳሴ ግድብ ገቢ ለማሰባሰብና የኢትዮጵያን አዲስ ዓመት ለማክበር በእንዲህ መልኩ ተሰባስበው በማየታቸው መደሰታቸውን ገልፀው ለፕሮግራሙ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አካላትን በተለይም ሁለት ዓመት ሊሆነው የተቃረበው የስቶክሆልም የታላቁ ህዳሴ ግድብ ምክር ቤትና ዘወትር ትብብር የሚያደርገውን የትግራይ ልማት ማኅበርን በማመስገን ኢትዮጵያ አገራችን በአሁኑ ጊዜ እያካሄደቻቸው ያሉ በርካታ ወገብ የሚያጐብጡ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በማውሳት ታላቁ የኀዳሴ ግድብ አሁን ያለበትን ደረጃ ለታዳሚው አብራርተዋል:: ወ/ሮ መብራት ከስቶክሆልም በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ መዛወራቸውን ገልፀው በዚህ ቆይታቸው ለስራቸው ድጋፍ ያበረከቱላቸውን አካላት በማመስገን ለእሳቸው የተቸራቸው ድጋፍ በበለጠ መልኩ አዲስ ለተመደቡት አምባሳደርም እንዲለገሳቸው በመጠየቅ በዚሁ አጋጣሚ ከኮሚኒቲው ተሰናብተዋል::





በዕለቱ በስቶክሆልም የታላቁ ኅዳሴ ግድብ ገቢ አሰባሳቢ ም/ቤት ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሃብታለም ገነት ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያውያኖች ልዩነታቸውን አጥበው ከአገራቸው ልማት ጐን በመቆም ሃገሪቱ በልማት እያስመዘገበችው ላለው ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

ፕሮግራሙ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተሰባሰቡበትና የኢትዮጵያ 2006 ዓ.ም. አዲስ ዓመት በደመቀ ሁኔታ የተከበረበት ከመሆኑ በተጨማሪ ኢትዮጵያውያኖችና ትውልደ ኢትዮጵያውያኖች ለታላቁ የኅዳሴ ግድብ ግንባታ ገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ነበር፡፡

የፕሮግራሙ ዓላማ ኢትዮጵያውያኖችን በጋራ በማሰባሰብ አዲስ ዓመትን ማክበር የነበረ በመሆኑ ፕሮግራሙ እንደታሰበው ከ450 በላይ ታዳሚዎች የተሳተፉበትና ታዋቂ አርቲስቶች ፍቅርአዲስ ነቃጥበብ፣ ተስፋዬ ታዬና ታዋቂዋ የሶማሊኛ ዘፋኝ ኒሞ ዳረን ሌሊቱን በሙሉ ታዳሚውን በማዝናናት ያነጉበት ዕለት ነበር፡፡ በዕለቱም ለታላቁ የኅዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ከ200,000.00 የስዊድሽ ክሮነር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ቆ.ጄ.ጽ/ቤት

ስቶክሆልም